የኢትዮጵያ አበይት ጉዳዮች መወያያ ሂደት

Ethiopian National Priorities Consultative Process

P.O.Box 171, East Lansing, Michigan 48823, E-mail: secretariat@enpcp.org


# በቺካጎ ስለ ተካሔደው ታላቅ የማሕበራዊ ድርጅቶች ስብሰባ

የኢትዮጵያ አበይት ጉዳዮች መወያያ ሒደት ተብሎ የሚጠራው አካል፤ ሐሙስ፤ ሰኔ ፳፰ ቀን ፪ሺ.፮ ዓ/ም (እ.ኤ.አ ጁላይ ፭ ቀን ፪ሺ.፲፬ ዓ/ም፤) በቺካጎ ከተማ፤ አሜሪካ፤ የመጀመሪያውን ታሪካዊ ስብሰባውን በተሳካ ሁኔታ አከናውኑዋል።

በስብሰባውም ላይ ማሕበራዊ (ሲቪክ) ድርጅቶችና ግለሰቦች የተገኙ ሲሆን፤ በርካታ ታዋቂ ምሑራንና ባላሙያዎች ጥናታዊ ገለጻዎች አቅርበዋል።

ገለጻዎቹ ያተኮሩባቸው አርእስቶች፤ ማሕበራዊ ድርጅቶች ስለሚጠናከሩበትና ለኢትዮጵያ ዲሞክራሲ፤ ለሰብአዊ መብት መከበር፤ ለሰላምና ለልማት ስለሚያደርጉት አስተዋጽኦ፤ ግጭትን ስለ መከላከልና ስለ መፍታት፤ ሐሳብን በነጻ ስለ መግለጽ እንዲሁም ስለ አገር ሉዓላዊነት አበይት ጉዳዮችን የሚያጠቃልሉ ነበሩ።

ተሳታፊዎቹ ማሕበራዊ ድርጅቶችና ግለሰቦች ከላይ በተጠቀሱትና በሌሎችም የሐገር ጉዳዮች ላይ ከተወያዩ በሁዋላ ባለ፲፰ ነጥብ ውሳኔዎች አስተላልፏል። (ዝርዝሩን በሒደቱ ድረ-ገጽ www.enpcp.org መመልከት ይቻላል።)

ከነዚህም ውሳኔዎች አንዱ ማሕበራዊ ድርጅቶችና ሌሎች አግባብ ያላቸውን አካላት በሰፋት የሚያሰባስብ ሐገራዊ ጉባኤ በተቻለ ፍጥነት እንዲዘጋጅ ለማድረግ ነው። በተጨማሪም፤ የፖለቲካና የሕሊና እስረኞች አሁኑኑ እንዲፈቱ፤ በግንቦት ፪ሺ.፯ ዓ/ም እንዲከናወን የታቀደው ብሔራዊ ምርጫ ነጻና ትክክለኛ እንዲሆን፤ አስፈላጊ ቅድመ-ሁኔታዎች እንዲሟሉ፤ ዓለም አቀፉ ሕብረተሰብና ወዳጅ ሐገር መንግሥታት፤ በኢትዮጵያ አምባገነንነትን በመደገፍ ፈንታ፤ ለዲሞክራሲ ግንባታ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን እንዲቆሙ ስብሰባው ጥሪውን አስተላልፏል።

በአጠቃላይም፤ ይህ ታሪካዊ ጅምር እየጎለበተና እየተሳካ እንዲሔድ ሌሎች ማሕበራዊ ድርጅቶች በሒደቱ እንዲሳተፉና ውሳኔዎቹን በሥራ ላይ ለማዋል ያልተቆጠበ ጥረት እንዲያደርጉ ትብብራቸውን በአክብሮት ይጠይቃል።